# <u>የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት</u>



**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡**

**የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ፣ የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ወዳጆች ሁላችሁም፡፡**

**እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ፡፡ ልሁል እግዚአብሔር እነሆ ፈጣሪያችን ፍጹም አምላክ ስሆን በፍጥረቱ የማይጨክን ርኅሩኅ የባሕርይ አምላክ እንደመኾኑ መጠን ሊያድነነን ስለፈቀደ ፍጹም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዷልና ዛሬ የልደቱን በዓል ለምናከብርባት ዕለት እንኳን አደረባችሁ፡፡ ወሰን የሌለውን ቸርነቱንና ምሕረቱን እያሰብን ፣ እግዚአብሔር አምላካችንን በፍቅር ፣ በሰላምና በአንድነት ሆነን እያመሰገንን መንፈሳዊውን ደስታችንን በማብሠር ነው፡፡**

**ሱባኤ ተቆጥሮ ፣ ትንቢት ተነግሮ ካለ በኋላ ማለትም ቅዱሳን ነቢያት ይመጣል ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ይወለዳል ብለው ተናግረው ከጨረሱ በኋላ መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት ቅድስት ድንግል ማርያምን አምላክ ከአንቺ ይወለዳል ብሎ አበሠራትና ጊዜው ሲደርስ ማለትም 5500 ዘመን ሲፈጸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተልሔም በተባለው ቦታ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ ኵነኔ ፣ ፍዳ ፣ መርገም ፣ ኀዘን ፣ ኃጢአት ሁሉ ተደመሰሰ፡፡**

**አንድነት ፣ ስምምነት ፣ ርኅራኄ ፣ ሰላምና ፍቅር ሰፈነ፡፡ ዕልል በሉ ይህን ያደረገላችሁን ፈጣሪያችሁን እግዚአብሔርን አመስግኑ በማለት አሁንም እንኳን ደስ አላችሁ ትላችኋለች እናታችሁ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡፡**

**<u>ጥያቄ</u>**

**ልደት ማለት ምን ማለት ነው?**

**<u>መልስ</u>**

**ልደት ብዙ ምሥጢር ይለበት ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ ከማኅፀን መወለድ ከጨለማ ወደ ብርሃን መውጣት ማለት ነው፡፡ <u>ምሥጢራዊ ትርጉሙም</u> ፣ ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት ፣ መኖር ፣ መፀነስ ፣ መወለድ ፣ ከእናት ኾድ ወደ ብርሃን መውጣት ፣ መገኘት ፣ ተገልጾ መታየት ነው፡፡**

ጥያቄ

የጌታችን ልደት ከሌላው በምን ይለያል?

መልስ

ሰው ሁሉ በአባትና በእናት መካከል በሚፈጸመው ሩካቤ ሥጋ ፣ (በሥጋ ግንኙነት) በዘርዓ ብእሲ ወብእሲት /በወንድና በሴት ዘር/ ምክንያት ተጸንሶ የሚወለድ ሲሆን ጌታችን ግን ይለአባት ፣ /ያለወንድ/ ያለ ዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፡፡

እንደዚሁም ሌሎች ሰዎች ልጅን ከወለዱ በኋላ ድንግልናቸው እንደማይኖር የታወቀ ስሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን አምላክን ከመጽነስዋ በፊት ፣ አምላክን በምትወልድበት ጊዜም ሆነ አምላክን ከወለደች በኋላም ሁሉ ጊዜ ድንግል ፣ ንጽሕት ፣ ቅድስት ናት፡፡ ስለዚህም የጌታችን ልደትና የእናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ድንግልና ፣ ንጽሕና እና ቅድስና ከሌሎች ሁሉ የተለየ ነው ማለት ነው፡፡

ጥያቄ

የመልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክትና የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ሁናቴ እንዴት ነበር?

መልስ

ወበሳድስ መርኀ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ ድንግል ሉቃ.1ü26፡፡

መልአከ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል የእግዚአብሔር አገልጋይ የኾነውን ካህን ኦሪት ዘካርያስን እግዚአብሔርን ወደሚያገለግልበት ቤተ መቅደስ ኼዶ ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ በእግዚአብሔር ፊት ደርሷልና አትፍራ መካን የምትባለው ኤልሳቤጥ ሚስትህም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዩሐንስ ትለዋለህ ይኸውም ፍጹም ደስታ ማለት ነው ብሎ ካበሠረው በኋላ በ6ኛ ወሩ ናዝሬት ገሊላ ወደነበረችው ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር ተላከ፡፡ ኼዶም እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን ከነፍስሽም ነፍስን ነሥቶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይሆናልና /አምላክ ከአንቺ ይወለዳልና/ በነቢያት ትንቢት ፣ በላእክት ተልእኮ ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ ተፈሥሒ ደስ ይበልሽ አላት፡፡

እርሷም ከዕንግዳ ሰላምታውና ከንግግሩ የተነሣ ለጊዜው ደንግጣ ነበር፡፡ ፍራትንና ድንጋጤን እያስወገደ ማብሠር ልማዱ የሆነ ቅዱስ ገብርኤል ግን ማርያም ሆይ አትፍሪ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በአንቺ ላይ ያድራል ኃይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ይለብሳል አምላክ ከአንቺ ይወለዳል አላት፡፡

ማርያምም ንጽሕት ፍጽምት ናትና ይህ ነገር እንዴት ይሆናል? እኔ እንደሆንኩ እንኳንስ የገቢር የኀልዮም የለብኝም፡፡ ለመሆኑ መሬት ያለዘር ስታበቅል ሴት ያለወንድ ስትወልድ የት አየህና ነው እንደዚህ የምትለኝ አለችው፡፡

መልአኩም መልሶ ከአንቺ የሚወለደው ፍጡር ተራ ሰው ሳይሆን ፣ ከአንቺ የሚወለደው ዕሩቅ ብእሲ ሳይሆን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ ወይም ከሥላሴ አንድ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ይህ የምነግርሽ ሁሉ ይሆናል አላትና እርሷም ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ እንደቃልህ ይሁንልኝ ይደረግልኝ አለችው፡፡

ከዚህ ብሥራት በኋላ ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ሆነ፡፡ እንደእኛ አቆጣጠር መጋቢት 29 ቀን ትስብእቱ ወይም ፅንሰቱ ሆኖ ታኅሣሥ 29 ቀን

ተወለደ ማለት ነው፡፡ ሙሉውን ወንጌለ ማቴዎስ 1ü18 እና ወንጌለ ሉቃት 2ü1 ጀምሮ ፣ መጽሐፈ ፍሬ ሕይወት በምህር ሰሎሞን ይመልከቱ፡፡

ጥያቄ

ለመሆኑ ጌታችን ለምን ተወለደ? የመወለዱ ዋና ምክንያትስ ምንድን ነው?

መልስ

በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ 1 ጀምሮ በተከታታይ ምዕራፎች እንደምንመለከተው ልሁል እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር ሰውን በአርአያውና በምሳሌው ፈጥሮ ከሁሉም ጥፍረት አልቆ አክብሮ በገነት አኑሮት ነበር፡፡ ዘፍጥረት 1ü26 ፣ 2üተ፡፡ ከዘሀምጋር ሕግንና መመሪያን ሰጥቶ ሕጉን እንዲያከብር አዝዞት ነበር፡፡

አዎ ይህን ዕፀ በለስ የበላህ እንደሆነ የኃጢአትን ሞት ትሞታለህና ዕፀ በለስን አትብላ ብሎታል፡፡ ይኸውም የፈጣሪና የፍጡር መለያ ፣ የአዛዥና የታዛዥ ልዩ ምልክት መሆኑ ነው፡፡ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ሕግና መመሪያ መኖሩንም የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ዘፍ.2ü16፡፡

ይሁን እንጂ ሰው /አዳም/ የፈጣሪውን ሕግና መመሪያን ጠብቆ በተፈቀደለት መሠረት መኖር ሲገባው የፈጣሪውን ሕግና መመሪያ ጥሶ ፣ የታዘዘውን አፍርሶ ያልታዘዘውን ሲፈጽም ፣ በልቡ አስቦ ፣ ተመኝቶ ይልተፈቀደለትን ያውም ከዐቅሙ በላይ የሆነውን የባሕርይ አምላክነትን ሲሻ /ሲፈልግ/ በመገኘቱ ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከገነት ወጥቶ ከክብር ወደ ሐሣር ተለውጦ መርገም ወድቆበት ከሕይወት ወደ ሞት ተባርሬ ነበር፡፡ ዘፍ.3ü1፡፡

በመሆኑም በአዳምና በሔዋን ላይ የወለደቀው መርገም ባለመነሣቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የነበረው 5500 ዘመን ሁሉ መርገሙን ሁሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ እስከ ደመሰሰው ድረስ የመርገም ፣ የፍዳ ፣ የጨለማ ፣ የችግርና የጭንቀት ዘመን ስለሆነ ሰው መልካምም ይሥራ ክፉ ኑሮው በሲኦል በችግር ውስጥ ሆኖ ነበርና ይህን ለመደምሰስ ተወለደ፡፡

አዎ በፍጥረቱ የማይጨክን የረኅራኄና የጽድቅ ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር አምላክ በአምስት ቀን ተኩል /ከመንፈቅ/ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎ ለአዳም በሰጠው አምላካዊ ተስፋ መሠረት ትንቢት ተነግሮ ሱባኤ ተቆጥሮ ካበቃ ፣ ጊዜው ሲደርስ ማለትም በነቢያቱ እንደበት ትንቢትን አናግሮ ከጨረሰ በኋላ 5500 ዓመተ ዓለም ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ ዘመኑም አምስት ቀን ያለው አምስት ሺህ ዓመት ሲሆን እኩል ቀን /መንፈቀ ዕለት/ ያለው ደግሞ አምስት መቶ ዓመትን ነው፡፡ ጠቅላለው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጥያቄ ፣ መልስ

ለመሆኑ የልደት ምሥጢር ምንድን ነው? ዛሬ የተሰበከው ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል ፣ በብርሃናተ ለቅዱሳን ፣ ወለድኩከ እምከርሥ እምቅድመ ኮከበ ጽባሕ ፣ የሚለው መዝሙርስ በውስጡ ምን ምሥጢርን ይዟል?

ሙሉ መልስ

ምስሌከ ቀዳማዊ በዕለተ ኃይል ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን በቅዱሳን ብርሃን ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከኾድ ወለድኩህ ይላል መዝ 109ü3፡፡

ይህ ቃል የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢርንም የያዘ እንደመኾኑ መጠን ፣ ሁሉን በሁሉ ስለ አሉ ማለትም የአብ ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ አንድነትንና ሦስትነትን ለመግለጽ ነው፡፡

ይህ መዝሙር አንድነቱን ሲገልጽ በፍጥረት ጊዜ ከአንተ ጋር ነበርኩ ፣ ቅድመ ዓለም ይለእናት መወለዱን ሲገልፅም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ አካል ዘእምአካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ ወለድኩህ የሚል ስሆን ፣ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ፣ ያለዘርዐ ብእሲ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ሲገልፅ ደግሞ የነቢያት ትንቢት በተፈጸመበት ፣ መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ በሚል ምሥጢር የልደቱን ዕለት ያበሥራል፡፡

ጥያቄ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ምን ዓይነት ስጦታዎች ተበረከቱለት? የእነዚህ ስጦታዎች ምሥጢርስ ምንድን ነው?

መልስ

ከቅዱሳት መጻሕፍቶዎችንና ከሊቃውንተ ብተ ክርስቲያን አባቶቻችን እንደምንረዳው ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል አምላክ እንደ ኾነ ለማጠየቅ ዕጣንን አመጡለት ፣ ንጉሥ እንደጫነ ለማየቅም ወርቅን አመጡለት ፣ እንዲሁም ማኅየዊ የሚኾን የሞቱ ምሳሌ ከርቤን አመጡለት፡፡

እነዚህ በሰብአ ሰገል የቀረቡ ስጦታዎች አምላካዊ ሥራዎችን የሚያመለክቱ ዐበይት ምሥጢራት አሉዋቸው፡፡ መዝ 71ü10

እነዚህ የፍጹም ሕይወት ፣ የአንድነት ፣ የሰላም ፣ የዕርቅና የፍቅር ምሳሌዎችም ምልክቶችም ሲሆኑ በውስጣቸውም እኛ በኅብረት በፍቅር ኾነን ፈጣሪያችንን ማመስገን እንደሚገባን የሚያስገነዝበን መልካም አርአያና ትምህርት ያለበት መልእክት አለው፡፡

ምክንያቱም የሰላም ምልክት ኅብረት በመኾኑ ፣ የሁሉም ኃጢኣት መደምሰሻ ፣ የመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ፣ የጽድቅ ማሰሪያ ደግሞ እውነተኛ ፍቅር ነውና፡፡

ጥያቄ

ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ በመላእክትና በሰው ምን ምስጋና ተደረገ?

መልስ

ጌታችን በብተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰዎችና መላእክት በአንድ ኾነው ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ፣ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃዱ በማለት እግዚአብሔርን አመስግነዋል፡፡

መሠረታዊ ትርጉሙም አምላክ ለሆነ ሥጋ ከሥላሴ ጋር በአንድነት ምስጋና ይገባዋል፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ግእዛኑን ወይም ነጻነቱን ይሰጠው ዘንድ በምድር ዕርቅ ተወጠነ ወይም ተጀመረ በዓለም ሰላም ሠፈነ ፣ በፈጣሪና በፍጡር መካከል ፣ በሰውና በመላእክት ፣ በፍጥረት ሁሉ ፍጹም ሕይወት ፣ አንድነት ሰላም ፣ ዕርቅና ፍቅር ሆነ ማለት ነው፡፡ ሉቃ. 2ü14፡፡

ጌታችን በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰማያት ተከፍተዋል ፣ መላእክት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ፈጣሪን እያመሰገኑ ከሰማይ ጌታችን ወደ ተወለደባት ወደ ቤተ ልሔም ጌታቸውን ለማመስገን ሲወርዱ ከምድርም ወደ ሰማይ ሲወጡ ይታዩ ስለነበር ትንቢት በተፈጸመበት መላእክት ባመሰገኑበት ቀን ወለድኩህ ይላል ዋናው የትርጉሙ ምሥጢር፡፡

አዎ ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ በመላእክትና በልሳነ ሰብእ (በሰው አንደበት) በፍጥረቱም ሁሉ እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድ ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

ተብሎ ተመሰገነ ፣ አብ ወላዲ ፣ ወለድ ተወላዲ ፣ መንፈስ ቅዱስ ሠራፂ እንደሆነም በፍጥረቱ በግልፅ ታወቀ፡፡

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምንም እንኳ ቀድሞሞ በነቢያት አንደበት ሲነገር ፣ በብሉያት ቅዱሳት መጻሕፍትም ሲመሠጠር እንደነበር ቢታመንም በልደቱ ምሥጢር ደግሞ በሥራ ተገለጠ፡፡ ጎልቶ ታየ ማለት ነው፡፡

ጌታችን ቤተ ልሔም በተባለው ቦታ በተወለደ ጊዜ ሰዎችና መላእክት በአንድ ኾነው ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እያሉ እግዚአብሔርን ማመስገናቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጹም ሕይወት ፣ የአንድነት ፣ የላም ፣ የዕርቅና የፍቅር አምላክ መሆኑን ያመለክታል፡፡

እኛም ያንን መሠረት በማድረግ ዛሬም ሁልጊዜም ጌታችንን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እናመሰግነዋለን፡፡ ቅዱስ ስሙ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን፡፡

እንግዲህ ልደትና የጌታችን ልደት በአጭሩ ሲገለጽ አሁን እንደተመለከትነው ነው፡፡

አዎ በገዛ ራሳችን ያመጣነውን ፍዳንና መርገምን ደምስሶ ከዲያብሎስ ክፉ አገዛዝ ነፃ ሊያወጣን መጣ፡፡ ከቅደስት ድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ ሕጉንና መመሪያውን አፍርሰን ፣ ትእዛዛቱንም ጥሰን በመገኘታችን በኃጢአት ብንወድቅም እርሱ ግን በፍጥረቱ የማይጨክን ርኅሩኅ ፣ ይቅር ባይ አምላክ ስለኾነ በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ ከወደቅንበት ሊያነሣን መጣ፡፡

አሁንም ቢሆን ሕጉንና መመሪያውን እንድንጠብቅ ትእዛዛቱንም እንድንፈጽም ታዝዘናል፡፡ አዎ ጌታችን የምትወዱኝስ ከሆነ ሕጌንና መመሪያዬን ጠብቁ ትእዛዜንም ፈጽሙ ፣ ሕጌንና መመሪያዬን የሚጠብቅ ትእዛዜንም የሚፈጽም ሁሉ አባቴም እናቴም ወንድሜም እኅቴም ነው ብሎናልና የእግዚአብሔር ወዳጆች መኾንን ከፈለግን የእግዚአብሔር ወገኖች ልንባል የምንወድድ ከሆነ ሕጉንና መመሪያውን መጠበቅ አለብን፡፡ ትእዛዛቱንም መፈጸም አለብን ማለት ነው፡፡

አዎ በሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ሮሜ.8ü3 ጀምሮ እንደምንረዳው እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር እንደሌለብንም ታዝዘናል፡፡

ጌታችን እንደነገረን ሥጋ ደካማ ነው፡፡ ሥጋዊ መንፈስ ተለዋዋጭ ነው፡፡ ሥጋ የሥጋን ፍላጎት ይመኛል፡፡ ቅዱስ መንፈስ ግን ጠንካራ ነው፡፡ የመንፈስን ፍላጎት ይመኛል፡፡ ሥጋ ኃላፊውንም ጊዜያዊውን ጥቅም ሲመኝ ቅዱስ የኾነ መንፈስ ግን የማይልፈውን የዘለዓለምን ሕይወት ይመኛል፡፡

ስለሆነም የዘለዓለም ሕይወት እንደሚገኝበት እንደመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ እንጂ እንደ ኃላፊው እንደ ጠፊው ጊዜያዊውን ጥቅም እንደሚመኘው እንደ ሥጋዊ መንፈስ እንደ ሥጋ ፈቃድ መኖር አይገባንም፡፡

አዎ በገላትያ ምዕ.4 ከቁጥር1 ጀምሮ እንደተነገረን የሥጋ ፈቃድ ተገዥዎች ከሆንን ነፃ አልወጣንም፡፡ አሁንም እዚያው ከባርነት ቦታ ነው ያለነው ማለት ነው ፤ የሥጋ ፍላጎት ብቻ ተዛዦች ከሆንን የዓለም ባሮች የርኵሰት ተገዦች እየሆንን ነው ማለት ነው፡፡

አዎ ወገኖቼ በዚሁ መልእክት ፣ በዚሁ ክፍል እንደ ተገለፀልን ጌታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ነፃ አውጥቶናልና ከእንግዲህ በኋላ የሰይጣን ባሮች የዲያብሎስ ተገዦች መኾን የለብንም፡፡ ስለ ኾነም በ1ኛ ዮሐንስ መልእክት ምህራፍ 4 ከቁጥር 7 ጀምሮ እንደተነገረን በእውነተኛው ፍቅር አንድ ሆነን ሕጉንና መመሪያውን ጠብቀን ትእዛዛቱንም እየፈጸምን እንኑር፡፡ ከበደላችን ሁሉ እንመለስ ፣ ንስሐ እንግባ ራሱ ጌታችን በማቴ.24ü36 እንዳስጠነቀቀን የሚመጣበት ሰዓት አይታወቅምና እኛ ራሳችን ከዚህ ካለንበት ጊዜያዊ ሥፍራ በሞት የምንጠራበትን ሰዓት አናውቅምና ኃጢአታችንን እየተናዘዝን ከማንኛውም የነውርና

የኃጢአት ተግባር ንጹሐን ኾነን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበልን ለመንግሥተ ሰማያት እንዘጋጅ ትላለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን፡፡

ለዚህ ያበቃን ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዓሉን የሰላም ፣ የአንድነት ፣ የፍቅርና የፍጹም ደስታ በዓል ያድርግልን፡፡ ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን ከዚህ ዕለትና ሰዓት አድርሶ ብርሃነ ልደቱን ላሳየን አምላካችን ምስጋና ይድረሰው አሜን፡፡

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ሰ/አሀ/ስ

መካነ ሕይወትመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ዋሽንግተን ዲሲ

2 ሺሕ ዓ.ም